# <u>ህዝባዊነት የሚለካው በተግባር ነው!</u>

ከጌታቸው ቀጀላ

የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ህአፓ) የኢትዮጵያን ህዝብ ማዕከል ባደረገ መልኩ ትግሉን የጀመረው ደርግ ሲመጣ፣ ወያኔ ስልጣን ሲወጣ፣ የፓልቶክ የወሬ ጥይት ሲንጣጣ፣ አይደለም። ድሮ በጣም ድሮ ለብዙዎች እውነት በተደበቀበት ሁሉም ገደል መስሎ በታየበት፣ ተስፋ ቆራጭነት ብቻ ሳይሆን ድንጋይ ዳቦ ነው ተብሎ በሚታመንበት፣ የታሪክ ገፅ የማይለወጥ ነው የሚሉ በበዙበት ወቅት ነው። ዓላማው ስልጣንን በግንዛቤ ለመግራት መሪዎችን ልጓም ለማስያዝ፣ ደሃው ከተሜን ገበሬውን መብቱን በእጁ ለማስጨበጥ፣ ለገዥዎች ምክርን ለነሆለለ ምሁር ተግሳፅን ለተዋዥዎች ንቃትን እንዲላበሱ ለማድረግ በተለያዩ መልኮች ማስተማር ነበር። “እኔ ያንተ አሽከር ያንተ ቡችላ” ብሎ ፎካሪን በራሱ ላይ ተመክቶ እንዲቆም “ለትግሉ ነው ህይወቴ” ብሎ እንዲዘምር ህዝብን መቀስቀስ ባስፈለገበት ዘመን ነበር። በተለይም የታችኛው ክፍል በራሱ ዕድል እያማረረ እንዳይኖር፣ በራሱ እንዲኮራ የራሱን ገድል እንዲዘምር በመምከር ነበር። ኢ.ህአፓ ኢትዮጵያ በዕኩልነት የሚኖሩባት ምድር፣ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ዕድል ወሳኞቹ እራሳቸው እንጂ የባዕዳን ማባበልና አጉል ዕርዳታ እንዳልሆነ የሚያስረዳበት የሚመክርበት ጊዜ እንደነበር ታሪኩ ያስረዳል። ያኔ ነው ትግሉ የጀመረው።

በትግል ዘመኑ የባዕዳንን ዳረጎት ተቀብሎ የተነሳበትን የህዝብ ዓላማ ክዶ ከጠላት አልወገነም ለባዕዳንም አላደረም። ያ! ነው የሀቀኛ ኢትዮጵያውያንን ድጋፍ የሚያስቸረው። በማጭበርበር የግል ጥቅም ለማስከበር ቢሆን ኖሮ መንገዱ ሌላ ነበር። አበዛኛው ከራሱ በላይ የመዋል አቅም ያለው ነበር። በዚህ በኩል ኢ.ህአፓን ለመኮነን የሚዳዳቸው አሳማኝ ነጥብ ሲያቀርቡ አይስተዋልም። የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ከመንዛት በስተቀር። ኢ.ህአፓ የህዝብን ስሜትና ሀቅ ሙጥኝ ብሎ በመያዙ ከህዝብ ጠላቶች ጋር ሁሉ ተጋጭቷል። በጦርም ሳይቀር ገጥሟል ተሰውቷል። ኢ.ህአፓን ከብዙ ፓርቲዎች ጋር የሚለየውም ያ! ነው። ህዝባዊ እምነቱን በቆራጥ ትግሉ ማስመስከር መቻሉ ነው። ለግለሰቦች ክብርና ነፃነት ያላሰላ በመሆኑ አቋራጭ መንጠልጠያዎችን ሁሉ መንገዴ ብሎ አይዛቸውም። በዚህም ነው ለስልጣን እንቆይ ሳይሆን በትግል ቀድመን እንሰዋ የሚሉ ታላላቅ መሪዎቹንና አባላቱን ያጣው። ኢ.ህአፓ የእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካን አስወግዶ በህዝብ ዐላማ ላይ ብቻ የሚያተኩርን ሲወድ ሲያስጠጋ ሲታገልና ሲያታግል ነው የቆየው/ የተስተዋለውም ያ! ነው። እኔንም ሆነ እኔን መሰሎች እንድንደግፈው የሚገፋፋን ይህ መሰሉ ተግባር ነው። የጀግና ደብር ነውና፣ ኢ.ህአፓ ጀግናን ያቀርባል እንጂ አያርቅም። ለሰላይ፣ ለቧጋች፣ ለከዳተኛ፣ ለሀገር ጠላት፣ ለህዝብ መብት ነጣቂ ግን እንቆቆ ነው ኢ.ህአፓ። ከቀረቡት የሚሽሩበት ከራቁት የማይፈወሱበት መድሃኒት።

ሆኖም ግን በየወቅቱ የሚነሱበት ጠላቶች መሰረታቸው ምንድነው ብሎ ለመረዳት ፈፅሞ ያስቸግራል። የህዝብን የወሳኝነት መብት የመቀበል ችግር ከሌለ በስተቀር በጠላትነት ሊሰለፉ የሚያስችላቸው ሀቅ የለም። ዳሩ ግን የተነሱበት ጠላቶቹ ሁሉ እንደጠ.ስ በነው ሲጠፉ እንጂ እስከዘለቄታው ቆመው ሲፋለሙት አልተስተዋሉም። እውነተን አል ያዙምና ነወ፣ ያለውን ህዝባዊ ትስስር ያልተረዳው ወያኔ የሬሳ ሳጥን በማውጣት ኢ.ህአፓን አስወግዛለሁ ብሎ አልሞ ነበር። ግን አልተሳካለትም። ኢ.ህአፓ የለምም ብሎ ነበር። የወያኔስ በጄ! ሌላው ምን ይሁነኝ ብሎ ነው ለጋራ ሀገር ልማትና ለገዛ ወገን በጎነት በሚጥር ወገን ላይ አሉባልታ ማራመድ ያስፈለገው። በኢ.ህአፓ ላይ ያልተሟሸ ተሳዳቢ ምላስ ያለመኖሩ ሀቅ የሚገለፀው ያንን ነው። ይሁን እንጂ እውነተኞች ከህሊናቸው ጋር የሚኖሩ በመሆናቸው የኢ.ህአፓን ተጋድሎ ለማካካስ ህሊናቸው አልፈቀድ ብሎ እውነቱን ሲመሰክሩ ይደመጣሉ። ይታያሉ። በመሪዎቹ ንቃትና የአመራር ችሎታ፣ በፓርቲ አባላቱ

ሀቀኛና ህዝባዊ ዐላማ፣ በህዝቡ ይሁንታ ባይታጀብ ኖሮ እንደምን ተብሎ ፓርቲው ሁሉንም በድል እየተወጣ ከዚህ ይደርሳል ተብሎ ይገመታል?

- በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት የዘመኑ ተማሪ ለአያቶቹ ምክር ለገሰ፣ መንገዱ ትክክል አይደለም ብሎ አለ፣ ሊያዳምጡ የፈቀዱ ግን አልሆነም። መጭው ዘመን እንዲያምር የሀገሪቱ ዕጣ ክፍል ሰላማዊ እንዲሆን ምክራችን ይደመጥ! ብሎ ሁሉም ነገር መስተካከል ይገባዋል ብሎ ጮኸ። ነገር ግን የሚሰማው ጆሮ አላገኘም። ይልቁንስ የበርካታ ተማሪዎች ዕጣ መጋዝና መታሰር ሆነ። በፖሊስ ቆመጥ መወገር በፖሊስ ጣቢያ ማደር፣ እያስመረረ መጣ። መጨረሻው ግን ለማይበጅ ሁኔታ መዳረግ ሆኖ ለመሪዎችም ለህዝብም ለሀገርም ያልሆነ ነገር ላይ ተደረሰ።

- የደርግ መንግስት በጉልበቱ ከስልጣን ላይ ተፈናጠጠ። በመጀመሪያው ሰሞን ይል የነበረው ወደ ባራኬ (ጦር ሰፈሬ) እመለሳለሁ የሚል ተስፋ ነበር። አብዛኛውም ድርጅት እዚያው እየተፈጠረ ከደረግ አብሮ ኢህአፓን ማውገዙን መረጠ። ትንሽ ብንታገስ ምናለበት የሚል ማዘናጊያ ቃል ይዘ ቀረበ። ኢህአፓ ግን አልተቀበለውም። የፖለቲካ ድርጅቶቹም በኢህአፓ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻቸውን ቀጠሉበት። ወታደሩ ሊስተካከል የሚችል በመሆኑ ሂሳዊ ድጋፍ ከተሰጠው ይሻሻላል ብለው ማቀንቀኑን መረጡ። ለኢህአፓ ግን መልሱ አንድ አንድ ብቻ ነበር። ወታደሩን በሙያው እናከብረዋለን ሀገር ለመምራት ግን ብቃት የለውም የሚል። ስለዚህም ከማህበረሰቡ የተውጣጣ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም! የሚል መፈክር አስተጋባ። ደርግ ሊሻሻል የሚችል ነው ያሉት ሀይሎች መኤሶንና ሌሎችም ፓርቲዎች፣ ገንቢ ሂስ በማቅረብ ማስተካከል ይቻላል ብለው ከደርግ ተጠግተው ሲሰሩ ስለነበር። ኢህአፓን ከዚህ አይነቱ ህዝባዊ ጥሪው ለመገደብ እርምጃ መውሰድ ጀመሩ። ወጣቱን እያሳዳዱ መግቢያ መውጫ አሳጡት። ብዙ ወጣት ቤቱን እየለቀቀ ተሰደደ፣ ብዙ መከራዎችን በኢህአፓ ላይ ለማድረስ በቁ። ይኸ ሀሰት አይደለም።

- ኢህአፓ ህዝብን በማደራጀት እምቢተኝነት እንዲጎለብት፣ የአርበኝነት መንፈስ በወጣቱ ዘንድ እንዲሰርፅ ሲጥር ሌሎቹም ደርግን ደግፈው እስከተወሰነ ጊዜ ከሄዱ በሁዋላ ደርግ ጉልበቱን አፈርጥሞ በሙሉ ዋጣቸው ወይም አባረራቸው። ሀቁ ያ ነው። ታዲያ ማን ነበር ቀደሞ እውነታውን የተናገረው? ኢህአፓ ወይስ ድርግን እንየው ያሉት ወገኖች? በገጠርም በጣም በርካታ ወጣቶችና የአካባቢው ገበሬዎች ተጠናክረው መታገል ሲጀምሩ። ኢህአፓ የስልጣን ሳይሆን የህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት እንዲከበር የሚፈልግ በመሆኑ ብቻ ነው የዘውድ ስርአትን ከሚቀበለው ግን በዲሞክራሲ ከሚያምነው የኢዲዩ ሀይል ጋር ሳይቀር ተባብሮ ለመስራት የሞከረው። በደርግ ላይ የኢህአፓ ምክር ተሰምቶ ቢሆን ኖሮ አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ባልተደረሰ ነበር።

- ሌላው ቀርቶ ደርግ እንደማይሆንለት ሲታወቅ ሀገርን ለነዚህ አራዊቶች ለቀህ ህዝብን ለመበታተን ሳታደርስ መሳሪያ ዕርዳንና ተባብረን መስመር እናስያዛቸው ብሎ ኢህአፓ ጠይቆት እንደነበር ይታወቃል። ደርግ ግን ከማን ጋር ከኢህአፓ ጋር? ብሎ ነው የመለሰው። ምን ያረጋል ፉከራውም ጥላቻውም አብረው ከሰሙ። ደርግ በቆላ ላይ እንደተገኘ የበረዶ ክምር ቀለጠ። ሀገርንም ህዝብንም ለመከራ ጥሎ አለፈ። ዛሬ አንዳንዶቹ የ

ኢህአፓ አውጋገሮች ቆራጡ መሪያችን እያሉ መንግስቱን ሲያጀጋንኑት የነበሩ የቀበሌና የፀጥታ ገራፊዎችና ታማኝ ካድሬዎች ለመሆናቸው አያጠራጥርም። ያም ሁሉ ሆኖ ግን ጊዜው የትብብርና ይቅር ለእግዜር የመባባያ ሰዓት በመሆኑ በጎሪጥ መተያየት የሚያስፈልገው አልነበረም። ሀቁ በሚነገርበት ሰዓት ግን ከወገናዊነት በፀዳ መልኩ ነገሮችን መመልከት ያስፈልጋል። ኢህአፓ ላይ ጠላትነታቸውን ያሳዩ ሁሉ አልተሳካላቸውም። እንደብረት አጥር በሀገሩ ላይ ካስማውን ተክሎ ነውና ያለው። የባዕዳንን ተንኮልም ቢሆን የተቋቋመው ያ በመሆኑ ነው። ዋናው ነገር ግን ከህዝብ ጋር መወገን በህዝብ ውስጥ መገኘት ያስገኘው ውጤት ነው እንደሌሎቹ አብረውት እንደጀመሩት ሁሉ ከምድረ ገፅ ሊጠፋ ያልቻለው። የጠላቶቹ ዕርግማን አለምልሞት ሳይሆን በዕቅድና በስልት በመጓዝ የህዝብን እውነታ ሀቄ ብሎ በመያዙ ነው። ይህንን ሀቅ ለየትኛውም ሁኔታ መለኪያው አድርጎ ስለያዘው ምናልባት የኢህአፓ ጠላቶች ሁልጊዜ የሚነሱት በዓላማ ላይ ሳይሆን ለግብ መዳረሻ በሚወስዱት እርምጃ ላይ በመሆኑ ከግባቸው ሳይደርሱ በራሳቸው ታክቲክ ተጠልፈው ወድቀው ይሆናል።

\- እኔ እንደሚገባኝ ኢህአፓ መሰረታዊ ለውጥን የሚፈልግ ድርጅት ነው። ስለዚህም ከጥገና ለውጥ አራማጆች ጋር አይስማማም። ጥገናዊ ለውጥ ፈላጊዎችም ከኢህአፓ ጋር አይግባቡም። ሆኖም ግን ግቡ ህዝባዊ መብት ከሆነ ሀቁ የሚታይ በመሆኑ ፍርዱን ለህዝብ መተው ነው የሚበጀው። በተቀረ ወያኔን ቅዱስ አድርጎ ያየ ወይም አስተምራለሁ ብሎ የሞከረ ውጤቱ ደርግ መኤሶንንና ሌሎች ተቃዋሚዎቹን እንዴት አድርጎ እንዳጠፋቸው የሚለይ ባለመሆኑ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ማለቱ፤ ከወያኔ መራቁ ይጠቅማል ብሎ መናገሩ፤ ወዳጅነት እንጂ! ጥላቻን ማስፋፋት አይደለም። እኔ ኢህአፓን የምደግፈው ካለፉት ተመክሮዎች የቀሰመ፤ የካበተ ልምድ ያለው በመሆኑ ነው። ወያኔን ሊቋቋም የሚችልበትን መንገድ ጠንቅቆ የሚያውቅ፤ ከወያኔ ጋር የማይሞዳሞድ፤ የባዕዳን አማካሪዎች ምክርም ሆነ ተግሳፅ የማይበግረው፤ በራሱ የሚያምን፤ ስለህዝብ መብት በመታገል የዳበረ ዕውቀት ያለው በመሆኑ ነው። ይህ እምነቴ ግን የሚመነጨው ከሀገሬና ከህዝቤ ፍቅር ላይ እንጂ ከድርጅት አምላኪነት ስሜት አይደለም። ሁሉም ሰው ለህሊናው ግልጽ ሆኖ ነገሮችን መፈረጅ ይገባዋል እላለሁ። የጥላቻ ፖለቲካ ለማንም አይጠቅምም።

ኢትዮጵያ በጠንካራ ልጆቿ መስዋዕትነት ተከብራ ትኖራለች!!

\-